# አልወለድም

**ደራሲ - አቤ ጉበኛ**
**አስተያየት - መስፍን ማሞ ተሰማ**

***መነሻ***




በተለያዩ ማህበራዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የረዥም ርቀት ጭውውት ከምናደርጋቸው ወዳጆቼ መኻል በቅርቡ ዳጎስ ያለ ፖስታ ደረሰኝ። ከፍቼ ስመለከተው የአቤ ጎበኛ አልወለድም መፅሀፍ ፎቶ ኮፒ ነበር።

እናም ዛሬ ላይ ሆኜ ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ህልውና አንፃር አቤን አነበብኩት። አንብቤ ስጨርስ ውስጣዊ ስሜቴን ከናንተ ጋር መጋራት ፈለግሁ። ብእሬን አነሳሁ። የሚከተለውንም ከተብኩ። እነሆ አልወለድም …

***መንደርደሪያ***

ፈረንሳዊው ደራሲ ቪክቶር ሁጎ ‘ሌ ሚዘራብል’ /ጎስቋሎቹ/ የተሰኘውን ድርሰቱን በ1962 (እአአ) ባሳተመበት ወቅት የሚከተለውን አስፍሮ ነበር።

“…በስልጣኔ መኻል ህይወት አምካኝ ሰው ሰራሽ ገሀነም እስካለ ድረስ …ሶስቱ ታላላቅ የዘመኑ መቅሰፍቶች፦ የሰው ልጅ በድህነት መዋረድ፤ የሴቶች በረሀብ መማቀቅ፤ የህፃናት ያለ እድሜያቸው መቀሰፍ፤ እስካሉ ድረስ …ድንቁርና እና ድህነት በምድር ላይ እስከተንሰራፉ ድረስ …እንደ ‘ሌ ሚዘራብል’ ያሉ መፃህፍት ጥቅማቸው አይሞትም።”

እንደምን ያለ ዘላለማዊ ቃል ነበር? አዎ! ረሀብና ምዝበራ፤በሽታና ድህነት፤ በዓለም ስልጣኔ መኻል ገሀነምና ገነት ወዘተ በህብረተሰብ ውስጥ እስካሉ ድረስ ‘ሌ ሚዘራብል’ ዘላለማዊ ድርሰት መሆኑን ትውልድ አሳልፎ፤ ዘመንን ተሻግሮ እንደ ትላንቱ ዛሬም እያስመሰከረ ይገኛል።

ሩሲያዊው ደራሲ ማክሲም ጎርኪ በበኩሉ ‘ማዘር’ /እናት/ በተሰኘው የ1907 ድርሰቱ በሩሲያ ውስጥ የዘመኑን ግፍ፤ በደልና የስርአቱን ኢፍትሃዊነት በሴት ሰራተኞች ገፀባህሪ ቀርፆ ለትውልድ አስተላልፏል። ይህን መፅሀፍ በ1966 ዓ/ም ማግሰት ኢትዮጵያ ውስጥ ያነበብን የዛን ዘመን ወጣቶች ምን ያህል የትግል ቋያ በውስጣችን አቀጣጥሎ እንደነበር በትዝታ የምናስታውስ ነው። ጎርኪ በህይወት ባይኖርም ‘እናት’ ዛሬም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የህብረተሰብ አካሎች ውስጥ ‘ግፍ አሻፈረኝ’ ብለው እንዲነሳሱ የማድረግ ሀይሉ አልደበዘዘም።

እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል በ1945 ያሳተመው ‘የእንስሳት አብዮት’ /አኒማል ፋርም/ በህዝብ መንግስትነት ስም ስልጣን ጨብጠው ፍፁማዊ አምባገነን የሆኑትን

የስታሊንን እና ተከታዮቹን የተበላሸ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዳደር እርቃኑን በማውጣቱ ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡ ውስጥ ያስከተለውንም የድህነት፣ የሽብር፣ የፍርሃትና የጨለማ ዘመን በገሀድ ከማሳየት አልፎ የመፅሀፉ ጭብጥ ዛሬም ቢሆን እውነታነቱ ደምቆና ጎልቶ ይታያል።

ለአብነት ያህል ከጠቀስኳቸው ሶስት የአውሮፓ ደራሲያን ዘመን ዘለል ስራዎች አልፈን ወደ አፍሪካ ስንሻገር **አልወለድምን** እናገኛለን። **አልወለድም** ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ጊዜና ትውልድ ያልከለለው (ምናልባትም ወደ እንግሊዝኛ ቢተረጎም በተመሳሳይ የግፍ አገዛዝ ቀንበር በመማቀቅ ላይ ለሚገኙ የአለም ህዝቦች ሁሉ የህይወታቸው መስተዋት የሚሆን) የህይወታችን ነፀብራቅ ሆኖ ይገኛል።

**አልወለድም** በግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የተፃፈና ታትሞ የነበረ ቢሆንም ቅሉ የመልእክቱ ይዘት አቤን ለመከራና ፍዳ፣ **አልወለድምን** ደግሞ ለእሳት ዳርጎታል። ይህንን አስመልክቶ በ1966 ዓ/ም ድጋሚ በታተመው አልወለድም መግቢያ ላይ አቤ ሲፅፍ፡-

*“ይህ መፅሀፍ /አልወለድም/ የዛሬ አስራ አንድ አመት ገደማ (1955 ዓ/ም) በደንቡ ምርመራ አልፎ ታትሞ በወጣ ጊዜ ታላቅ ችግር ፈጥሮብኝ ነበር። ከአንድ አመት በላይ ሲያጨቃጭቀኝና በየቦታው ሲያስጎትተኝ ቆይቶ በመጨረሻ በእሳት ነዶ የሰማእትነት ፅዋውን እስከተቀበለበት ድረስ ብዙ የክርክር መልሶች እንድፅፍለት አስገድዶኛል። በፖሊስ አሳስሮኛል። ብዙ ጠላቶችም አፍርቶብኛል።”* ይላል

ዛሬ ላይ ቆመን የአልወለድምን እድሜ ስናሰላው (መጀመሪያ ከታተመበት ዘመን አንስቶ) ግማሽ ምእተ ዓመት ሊሞላው ነው። ሃምሳ  ዓመት! ከ አራት አስርታት በፊት ከሰው ልጆች ሰብአዊ መብቶች ከሆኑት አንዱ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቱን አቤ ተነፍጎ ለእስርና ለእንግልት ሲዳረግ መፅሀፉም እንዳይሰራጭ ታገደ።

ይህንን ስሌት የሚያነብ ኢትዮጵያዊ በዚህ ቅፅበት በአእምሮው ውስጥ የሚደውል ታላቅ ጥያቄ ይኖራል። የሚከተለው፡-

ለመሆኑ በዚህ ዘመንና በዚህ ትውልድ በምትገኘው ኢትዮጵያችን የምንኖረው የዚህ ዘመንና የዚህ ትውልድ ዜጎች ቢያንስ አቤ ከግማሽ ምእተ ዓመት በፊት ደርሶበት ከነበረው የሰብአዊ መብት እጦት ስቃይና እንግልት ተገላግለናልን?!

እነሆ ከዚህ አንድ ዘለላ ጥያቄ ተነስተን **አልወለድምን** ስንመረምር አቤ ባንድ ትውልድ ውስጥ ኖሮ ያለፈ ደራሲ ሆኖ አናገኘውም። **አልወለድም** ትውልድን አሳልፎ፣ ግምሽ ምእተ ዓመት ላይ ቆሞ ዛሬ ላይ ሀገራችንና ህዝባችን የሚገኙበትን እውነታ እንደ ትርኢት እንድንመለከት ያስገድደናል።

እንደ ሁጎ፣ እንደ ጎርኪ፣ እንደ ኦርዌል ስራዎች ሁሉ አልወለድም በዘመን፣ በትውልድና ምናልባትም (ቢተረጎም) በድንበር አጥር ያልታሰረ፣ የኢፍትሃዊ አስተዳደርን ምንነት ያለፈ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የዛሬንም የህብረተሰብና የመንግስት ግንኙነት እውነታን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ዘመን አይሽሬ ድርሰት ሆኖ ይገኛል።

**አልወለድም** በዘመን ዘለልነቱና በጭብጡ ከላይ ከተጠቀሱት ታላላቅ ድርሰቶች ጎን ብናስቀምጠውም በተለይ ግን ከኦርዌል የእንስሳት አብዮት ጋር ማነፃፀር እንችላለን።

የኦርዌል የእንስሳት አብዮት እና የአቤ አልወለድም ተመሳሳይነትም ልዩነትም አላቸው። ለምሳሌ የእንስሳት አብዮት ተምሳሌያዊ /ሲምቦሊክ/ የአፃፃፍ ዘዴን እንደመጠቀሙ ሁሉ በአልወለድም ውስጥም ይህንን ዘዴ እናገኛለን። የእንስሳት አብዮት ጭብጥ በስርአተ ማህበርና በስርአተ መንግስት ውስጥ ያለውን ህብረተሰባዊ አስተዳደር ሲመረምር፤ የአልወለድም ጭብጥም ይኸው ሆኖ ይገኛል።

በሌላ ወገን የእንስሳት አብዮት በእንስሳት ገፀ ባህሪያት የተዋቀረ ሲሆን አልወለድም ግን ሰዋዊ ባህሪያትን ይዞ ይገኛል። የእንስሳት አብዮት ትርክት ሂደት ሙሉ ለሙሉ ለ አንባቢያን ምናባዊ ግልቢያ የተለቀቀ ሲሆን አልወለድም ግን በከፊል የአስተማሪነት ባህሪን ተላብሷል።…የአልወለድም ሆነ የእንስሳት አብዮት የጭብጦቻቸው ወቅታዊነት በተለይ ለ እኛ ለኢትዮጵያዊያን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዛሬ ጎልቶ ይገኛል።

በቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የአልወለድም ጭብጥ እውነት ነበር። በኮሎኔል መንግስቱ ሃይለ ማርያም ኮሚኒስታዊ አገዛዝ አልወለድም እውነት ነበር። በአቶ መለስ ዜናዊ ጎጠኛ አገዛዝ አልወለድም እውነት ነው።

እነሆ ዘውዳዊውናን ኮሚኒስቱን ስርአቶች አልፈን ዛሬ ላይ ከምንገኝበት ሶስተኛው የ አገዛዝ ስርአት አንፃር እውነታውን ለመቃኘት ይረዳን ዘንዳ የሚከተለውን ጥልቅ አገላለፅ ከአልወለድም ጠቅሰን ወደ ዋናው ቅኝታችን እንዘልቃለን።

*"የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ ቅን ጎዳና ለመመራት በተዘጋጀበት ጊዜ ቅን አላማውን ጠማማ ለሆነው የግል ፍላጎታቸው ለመሰዋት የተዘጋጁ አራዊት በየክፍሉ ተለቀቁበት።*

*ተዘረፈ፤*
*ተዘርፎም ተገረፈ።*
*ራሱ ተበደለ፤*
*ራሱ ተገደለ።"*

አዎ! እውነት ብለሃል አቤ! ዛሬም ዘመን ያልሻረው ሃቅ ነው!!

## ኢ.ይዝራኤሎስ - አቃኒዮ

ታሪከኛው አልወለድም ራሱ እንደነገረን ከሆነ የትውልድ ሀገሩና ዋና ከተማዋ በገሀዱ ዓለም የምናውቃቸው ሆነው አናገኛቸውም። እንደታላላቆቹ ፀሀፍት እንደነ ኦርዌል ሁሉ አቤ በአልወለድም ያስተዋወቀን ሀገርና ከተማ ግና የራሳቸው ተምሳሌነት /ሲምቦሊዝም/ አላቸው።

*"እኔ የተወለድኩት ኢ.ይዝራኤሎስ የተባለችው ደሴት በወራሪዎች ስትበዘበዝና ስትጠቃ ስትገዛም ኑራ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ ራሷ የተበላሸች ሀገር ነበረች። ይህች በታላላቅ ውቅያኖሶች የተከበበች ሀገር ዋና ከተማዋ አቃኒዮ የምትባል ሲሆን እኔም የተወለድኩት በዚህችው ከተማ ነው።"* ይለናል።

አልወለድም ልቦለድ ነውና እኒህ ስፍራዎች የደራሲው የፈጠራ ውጤቶች /ከሳንሱር ለመዳን/ ቢሆኑም የሚወክሉት /ሲምቦላይዝ የሚያደርጉት/ በገሀዱ ዓለም የምናወቃትን ሀገራችንን ኢትዮጵያንና ዋና ከተማዋን አዲስ አበባን ነው።

*"ነፃነቷን ካገኘች በኋላ እራሷም የተበላሸች ሀገር ሆናለች"* ይላል አቤ ሲፅፍ። ይህ የሚያመለክተን ፋሽት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለሁለተኛ ጊዜ ወርራት ለአምስት አመታት ከተቆጣጠረቻት በኋላ በ1933 ዓ/ም ነፃነቷን መልሳ ብትቀዳጅም ከነፃነት ወዲህ የነበረው የግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ አስተዳደር እየተበላሸ የመጣ መሆኑን ነበር። የዘውዳዊው አገዛዝ ብልሹነት በኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ኮሚኒስታዊ አገዛዝ ብሶበት በዛሬው የአቶ መለስ የህወሃት አገዛዝ ደግሞ መረን ለቆ ይገኛል።

*"... ለሁሉ እኩል ተብሎ የተደነገገው ህግ እንኳ ባፈፃፀሙ እንደ ሰዎች ሁኔታ የሚሄድ ነበር"* ይላል አያይዞ። ይህ እውነታ የዛሬ ሃምሳ አመት የነበረ ቢሆንም ዛሬ ግን ከመቼውም ግዜ በላይ አፍጥጦ የሚታይ የኢትዮጵያ ገዢ ሃይሎች መለያ ባህሪ ሆኖ ይገኛል።

*"አብዛኛው የሀገሪቱ ተወላጆች በእኩልነትን በነፃ የሚያገኙት አየርንና የፀሀይ ብርሃንን ብቻ ሲሆን የቀረውን ነገር በመጠኑ እንኳን ለማግኘት ብዙ ድካምና ራስን ለባርነት አሳልፎ መስጠት ነበረባቸው"* በማለት በኢይዝራኤሎስ ውስጥ ከግማሽ ምእተ አመት በፊት ሰፍኖ የነበረውን የህዝብና የሀገር ሀብት በጥቂቶች ቁጥጥር ስር የመዋሉንና የዜግነት እኩልነት የይስሙላ መሆኑን በምሬት ይገልፃል።

እነሆ ዛሬ በአብዛኞቻችን እድሜ ሶስተኛው የመንግስት አይነት ላይ ሆነን ከግማሽ ምእተ አመት በኋላ ምን የተለወጠ እውነታ ላይ እንገኛለን? በዚህ ዘመንና ወቅት የ ኢትዮጵያዊያን የዜግነት እኩልነት እጅግ  አፓርታይዳዊ አይደለምን?

አዎ የዛሬዋ ኢትዮጵያ በታሪኳ ታይቶ በማይታወቅ የጎጥ ፖለቲካ በአንድ ብሄረሰብ ፍፁም አምባገነናዊ አገዛዝ ስር ወድቃ ትገኛለች። ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት አዛዥ እስከ ወታደራዊ የበላይ መኮንኖች፣ ከመንግስት ተቋማት ባለስልጣናት እስከ ክፍለ ሀገር፣ ወረዳና ቀበሌ አስተዳዳሪዎች *የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ* አባሎች አይደሉምን?

በዚህ ዘመንና ወቅት ኢትዮጵያዊያን "የሀገሪቷን አየርና ፀሀይ ብርሃን" እንጂ በ እኩልነት የሚጋሩት፣ ሀብቷንና ፀጋዋን ግን የበይ ተመልካች ብቻ አይደሉምን? በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ምርታማ የእርሻ መሬቶች ለባእዳን ሀብታሞች ለሃምሳና ለመቶ አመት ዝርፊያ እየተቸበቸቡ ገበሬው በገዛ ሀገሩ ለባእዳኑ ዘራፊዎች ባርያ እንዲሆን ተደርጎ የለምን? የዛሬይቷ ኢትዮጵያ ከሃምሳ አመት በፊት ከነበረችው ኢይዝራኤሎሰ ብሳለች ወይስ ተሽላለች?

## <u>አልወለድም ለምን አይወለድም?</u>

በሀገረ ኢይዝራኤሎስ በአቃኒያ ከተማ በልመና ተዳዳሪ ከሆነች አንዲት ድሃ ሴት ማህፀን የተፀነሰው ህፃን የነፃነትና የፍትህ ጥያቄዎችን አንግቦ 'አልወለድም' በማለት ማመፅ የጀመረው እናቱ ሆድ ውስጥ ሆኖ ነበር። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

*"አንድ ሰው ሲያልፍ ስለ መድሃኔአለም አለችውና /እናቱ መሆኗ ነው/ ሳንቲም ሲሰጣት ከእጅዋ ላይ ከነበረው ሌላ ሳንቲም ጋር ተጋጭቶ ቅጭል ሲል በሆዷ ውስጥ ከተኛሁበት ብንን አልሁ። ከእንቅልፍ መንቃት ብቻ አይደለም፣ ከድንቁርና ስሜትም ነቃሁ።"* ይላል አልወለድም ገና ሳይወለድ።

የሳንቲሞቹ መቃጨል የእውቀት ብልጭታ ተምሳሌ መሆኑ ነው። ለሶስት ሺህ ዘመን አንቀላፍታ ነበር የምትባለው ኢትዮጵያ ከምእተ አመታት እንቅልፏ ለመንቃት በጃንሆይ

ዘመን የስልጣኔ ጭላንጭል እየታየባት ነበር። በዛን ዘመን የሳንቲሞቹ መጋጨት ሲምቦሊዝም በአሮጌው ስርአት እና በአዲሱ ስልጣኔ መካከል ያለውን መጋጨትም አመላከች ነበር። በግጭቱም የተፈጠረው እውቀት ኢትዮጵያ ከጨለማ ወደ ብርሃን የመሸጋገሪያ ሂደት ላይ እንደነበረች የሚያሳይ ይሆናል።

ህፃኑ የለውጥ /ብርሃን/ ፈላጊው ትውልድ ተምሳሌ ነበር። *"...ከእንቅልፍ መንቃት ብቻ አይደለም፣ ከድንቁርና ስሜትም ነቃሁ"* ይላል ያልተወለደው ህፃን። የታምረኛው ህፃን እናት ድርብ ተምሳሌነት ኢትዮጵያን የሚወክል ነው። ህፃኑም በምድረ ኢትዮጵያ የተወለዱትን ለውጥ ፈላጊ ወጣት ትውልድ ወካይ ሆኖ ነው የቀረበልን። ይህም የአቤን ከ አድማስ የዘለቀ ራእይ ያሳየናል።

ጉደኛው ህፃን መወለጃው በተቃረበ ጊዜም መከረኛ እናቱ ጉድ እስክትልና 'ሰይጣን' የሚያናግራት እስኪመስላት ድረስ 'አልወለድም' ሲል ሙግት ገጠማት። እንዲህ እያለ፦

*"ታዲያ ለምን አትወለድም?" አለች።*

*"ተወልጄ በችግር መሰቃየት አልፈልግም።"*

*"እኔ በተቻለኝ መጠን አሳድግሃለሁ።"*

*"ሊያኖረኝ የሚችል ሀብት አለሽ?"*

*"እንደዚሁ ለምኜም ቢሆን አሳድግሃለሁ።"*

*"ሞት ይሻላል!...ልመናን ተማምኜ ነው የምወለድልሽ? በገዛ ሀገርሽ ላይ የምትችይውን ሰርተሽ በመኖር ፈንታ እንዴት ልመናን ተስፋ አድርገሽ ትኖሪያለሽ? ያንቺ በዚህ ሁኔታ መነሳቆል አንሶ ደግሞ ማደሪያ ሌለው ልጅ ለምን ትወልጃለሽ?"*

ይህ ከሀማሳ አመት በፊት አልወለድም ብሎ እናቱን የሞገታት ህፃን ያነሳቸው ጥያቄዎች የአንባቢን ህሊና ጓዳ ሰቅዘው የሚይዙ እውነታዎች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ብሰውና ንረው እንጂ ቀንሰው ወይም ተሻሽለው አናገኛቸውም።

እናቱ ለማኝ ነች። እንቱ የኢትዮጵያ ተምሳሌ ነች። ለማኚቱ እናቱ ዛሬ በልመናዋ በ አለም የታወቀችው ኢትዮጵያ ነች። ልመናን ባህሏ ባደረገችው ኢትዮጵያ ውስጥ ልመናን እንደ እናቱ ተስፋ አድርጎ ለመኖር አልወለድም አለ፣ የዛሬ ሃምሳ አመት! ሙግቱን ይቀጥላል ህፃኑ፦

*"እሺ መሬት አለሽ?"*

*"የለኝም"*

*"ቤት አለሽ?"*

*"የለኝም"*

*"ታዲያ ምን አለሽ?"*

*"ምንም የለኝም።"*

እዚህ ላይ ደግሞ እናቱ የኢትዮጵያን ሰፊ መከረኛ ህዝብ ትወክላለች። ዛሬ ባላባትና መሳፍንት የለም። ዛሬ የኢትዮጵያ መሬት የባእዳን ቱጃሮች ሀብት ሆኗል። ዛሬ ገባር የለም። ዛሬ ለባእዳን እንደ ባሪያ የሚለፉ ገበሬ እንጂ! ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ከመቼውም ዘመን በከፋ ምንም የለውም። ያጣ የነጣ ድሃ ሆኗል። ተመፅዋችና ለማኝ!! ጥቂቶች ግን ገነት ውስጥ ይኖራሉ!

ትረካችንን እንቀጥል።

*"ታዲያ ድህነትን፣ በሽታንና ድንቁርናን ልታወርሺኝ ነው ተወለድ የምትይኝ?"*

*"እድልህን እንዴት ታውቀዋለህ ልጄ?"*

***"ቀማኞችና ነፍሰ ገዳዮች፣ እንዲሁም የነፃነት ጠላቶች በሰለጠኑበት ደግሞ ምን እድል አለ? የድሆችን ልጆች የሚጠብቃቸው የወላጆቻቸው መከራና ችግር ብቻ ነው። መከራና ችግርን ከድሆች ትከሻ ለማውረድ እንደኔ ከሆድ ውስጥ ጀምሮ ለመብትና ለነፃነት መሟገት ያስፈልጋል።"***

ይህ ቀለበታዊ እውነታ ከትውልድ ትውልድ መሽከርከሩን የሚያቆመው መች ይሆን? የሚያቆመውስ የትኛው ትውልድ ነው? አዎ! ሀገራችን በድህነት፣ በበሽታና በድንቁርና ተተብትባ ከአንድ የከፋ የአገዛዝ ስርአት ወደ ሌላ የባሰ የአገዛዝ ስርአት በቅብብሎሽ እየተላለፈች እነሆ ዛሬ ላይ ደርሰን "ቀማኞችና ነፍሰ ገዳዮች እንዲሁም የነፃነት ጠላቶች በሰለጠኑበት ዓለም ምን እድል አለ?" ብሎ ከተሟገተው አልወለድም የዚህ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በእንደ ምን ያለ መልኩ ይሆን ተሽለን የምንገኘው?

የአልወለድምን ላለመወለድ ሙግት እውነታ ከሃምሳ አመት በኋላ ዛሬ ለምናነብ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሚያሳፍርና የሚያሸማቅቅ አይደለምን?

ቀማኞችን፣ ነፍሰ ገዳዮችንና የነፃነት ጠላቶችን ከኢትዮጵያ ማንቁርት ላይ የምናላቅቀውስ መቼ ይሆን? በዚህ ትውልድ? በሚቀጥለው? ወይስ…

## <u>አልወለድም ተወለደ</u>

*"እባክህ ስለ ፈጠረህ ብለህ ተወለድ?"* ስትል ተማፅናው ነበር ድሃዋ፣ ለማኟ፣ በረንዳ አዳሪዋ እናቱ። እሱ ግን …

*"… እኔን ወደ ባርነት ግባ ሲሉኝ ታላቅ ፀብ መፈጠሩ ነው! 'አሻፈረኝ ለባርነት አልወለድም' ብሏል በይ! ሰውን ለመወንጀልና እንቢተኛ ነው ለማለት ዳኛ ሞልቷል። ዳኛ የማያገኙት ለነፃነት የሚሟገቱት ናቸው እንጂ ነፃነት ፈላጊዎችን ለመክሰስ የዓለም ፍርድ ቤቶች ሁሉ ክፍት ናቸው። ክሰሺኝ። 'እምቢ ብሏል' በይ!"* ሲል መልሶላት ነበር።

ይህ ትንቢት ነው። ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ በነፃነትና በባርነት መካከል ስለሚጠብቀው ፍልሚያ የተነገረ ትንቢት! "… ዳኛ የማያገኙት ለነፃነት የሚሟገቱት ናቸው እንጂ ነፃነት ፈላጊዎችን ለመክሰስ የዓለም ፍርድ ቤቶች ሁሉ ክፍት ናቸው…" የሚል ትንቢት!

ይህንን ትንቢታዊ ቃል አፈፃፀሙን በእድሜያችን ባየናቸው ሶስት ስርአተ መንግስታት በተለይም በደርግና በኢህአዴግ አገዛዞች ዙሪያ እንተንትን ብንል መፅሀፍ ሳይሆን መፃህፍት ይሆንብናል። ግና ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ፣ ልቡናም ያለው ልብ ይበል ብሎ አቤ የዛሬ ሃምሳ አመት ነግሮን ነበር! እስካሁን ግን የሰማነው አንመስልም ወይም ሰምተንም ከሆነ ለውጥ ማምጣት አልቻልንም። ራሳችን የራሳችንን መቃብር እየቆፈርንና ራሳችንን በጉርጓዱ እየቀበርን እነሆ ከአልወለድም ወዲህ ሃምሳ አመት ሆኖናል።

የአልወለድም እናት አመፀኛ ልጇን ግን ከሳው ፍርድ ቤት አላቀመችውም። ይልቁንም ለጉስቁልናዋ፣ ለድህነቷ፣ በጨለማ ህይወት ለመማቀቋና ለባርነቷ ከናካቴው መወገድ ይህ የሚሞግታት ፅንሷ ምክንያት ሊሆን ይችላል ብሎ ውስጢ አምኗል።

*"እሷም በመጥፎ እድሏ አምርራ ታለቅስ ጀመር። ያለቀሰችውም ጥቅሙን ያላወቀችው የነፃነት ነበልባል የሚያነደኝ ፅንስ በሆዷ ስላገኘች እንጂ በርግጥ የበደላትን መከረኛ ኑሮ በማስታወስ አልነበረም"* ይለናል አልወለድም።

የነፃነት ነበልባል የሚያነደው ፅንስ ደግሞ የተፈጥሮ ህግ ነውና መወለድ ነበረበት። እና አልወለድም በአመፅ ተወለደ። የተወለደውም በኦፐራሲዮን! ኦፐራሲዮኑ የእናቱን /የ ኢትዮጵያን/ ድርብርብ ስቃይ ያመለክተናል፣ ወይም ሲምቦላይዝ ያደርጋል።

## <u>አልወለድም ማን ነው?</u>

አልወለድም መጠሪያ ስም የለውም። የተለየ መልክና ቁመናም አልተሰጠውም። የዘር ታርጋም አልታተመበትም። አልወለድም ተምሳሌያዊ /ሲምቦሊክ/ ገፀባህሪ ነው። በስቃይ ተወልደው በስቃይ የሚኖሩትን የኢትዮጵያን ልጆች ሁሉ ይወክላልና። ኦሮሞውን፣ ትግራዩን፣ አማራውን፣ ሲዳማውን፣ ሀረሪውን፣ ጉራጌውን፣ አኝዋኩን፣ አፋሩን፣ በጥቅሉ የጦቢያን ልጆች ሁሉ!

ነፃነታቸውንና ሰብአዊ መብታቸውን ተገፈው፣ በድህነት ወለል ላይ ተጥለው በግፍ አገዛዝ የማቀቁትንና 'እንቢ ለባርነት! እንቢ ለግፍ አገዛዝ!' ብለው በግፈኞች እጅ መራራ ፅዋ ለተጎነጩት የኢትዮጵያ ልጆችም በሙሉ ተምሳሌያዊ ገፀ ባህሪ ነው አልወለድም።

እንዴት? ቢሉ፦ አልወለድም ለነፃነትና ለሰብአዊ መብት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ እንደተሟገተ ታሰረ። ታስሮም ለፍርድ ቀረበ። ለፍርድ ቀርቦም ፍትህ አጣ። ፍትህ አጥቶም ሞት ተበየነበት። እና ግንባሩን በጥይት ነድለው ገደሉት።

ታዲያስ?! ባለፉት ሃምሳ አመታት እንዲህ ያለ አሟሟት የሞቱት ስንቶች ናቸው? ታዲያ አልወለድም እነዚህን ሁሉ አልሆነምን? አልወለድም የትላንት የነፃነት ፋኖዎችን ብቻ አይደለም የሚወክለው። የዛሬዎቹንም ጭምር እንጂ።

*"ወላጆቼ ወይም ፈጣሪዬ ወደዚህ አለም እንድመጣ ፈልገው እንደሆን አስቀድመው ወደ አለም መጥቼ ከአለም እስክወገድ ድረስ በሰላም፣ በፍቅር፣ በደስታ ከሁሉም ይልቅ በነፃነት ልኖር የምችልበት እድል ማዘጋጀት ነበረባቸው። ይህንን ስላላገኘሁ ግን በአመፅ ተወልጄ በአመፅ ሞትሁ"* ይለናል የአልወለድም መንፈስ ስለደረሰበት ምድራዊ ስቃይ ሲያጫውተን።

አንተ ማን ነህ? ብለን አንጠይቀውም። ምክንያቱም እሱ በእኛ ውስጥ ያለው እኛ በመሆኑ። ምክንያቱም ዙሪያ ገባችንን ስንቃኝ በአካለ ስጋ የምናውቃቸው አልወለድሞችን ከጎረቤት፣ ከትምህርት ቤት፣ ከመስሪያ ቤት፣ ከፋብሪካ፣ ከገጠር፣ ከከተማ እንገኛለንና!!

## አልወለድምና ትግሉ

አልወለድም ከስርአቱ ጋር ያደረጋቸውን የትግል ዘርፎች በመተንተን በተለይ ከደርግና ከ ኢህአዴግ አገዛዞች ጋር ተምሳሌነቱን እያነፃፀርን እንፃፍ ብንል አያሌ ጥራዛት ያሉት መፅሀፍ ይወጣዋል። የአልወለድም ታላቅነትም እዚህ ላይ ነው። ታዲያ ከቁና ሙሉ የ አልወለድም የትግል ዘርፎች በዚህ ቅኝት መቅረብ የሚችለው በማንኪያ ብቻ ጨልፎ ማቅመስ ይሆናልና እነሆ ቅምሻ...

### ሀ. አልወለድማና ምሁር

ከእናቱ ማህፀን በኦፐራሲዮን የተወለደው ህፃን መጀመሪያ የተጋጨው ከአዋላጁ ዶ/ር ጋር ነበር። ነፃነት ወደሌለበት አለም ለምን እንድወለድ አደረከኝ በማለት። "ስለነፃነትና መበት እንደምን ማወቅ ቻልክ?" ይለዋል ዶ/ሩ ወደ አለም በልቅሶ የመጣውን ህፃን።

*"እናንተ በአካል ብቻ የምታምኑ! የነፃነት ፍቅር በአስተማሪና በግዙፍ አካል ብቻ ሳይሆን ህይወት ካለው ፍጡር ሁሉ ጋር ተቀላቅሎ የሚፈጠር ነገር ነው። አውሬው ሲያቆስሉት እጅግ የሚበሳጨውና ታላቅ ጀብዱ የሚሰራው፣ እንስሳው ልረድህ ሲሉት የሚፈራገጠው በእናንተ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ስለነፃነት ጥቅም ያስተማረው ኖሮ ነው? የነፃነት ስሜት በደም ህዋሳት ሁሉ ተሰራጭቶ አብሮ የሚፈጠር ነገር ነው። ይልቁንም በተንኮል የተፈጠሩ ትምህርቶችና ስብከቶች ፍጡር ሁሉ በተፈጥሮ ያገኘውን የነፃነት ስሜት እየደመሰሱ ወደ ባርነት የሚያስተላልፉ ጠንቆች ናቸው።..."* ሲል ይመልስለታል አልወለድም።

ዛሬ በአይናችንም የምናየው፣ በጆሯችንም የምንሰማው እንደምን ያለ ዘመን ያልሻረው ሀቅ ነው?! በምሁራኑ አስተሳሰብና በብዙሃኑ እምነትና ትግል ዙሪያ አልወለድም ያቀረባቸውን በርካታ ጥልቅ ነጥቦች ለመፅሀፉ አንባቢያን ትቼ ወደሚቀጥለው ነቁጥ ባመራስ?

### ለ. አልወለድምና ሃይማኖት

*"... በማንኛውም የሃይማኖት አስተማሪ እንደበት ሲነገር ያገኘሁት አንድ ያልተለወጠ አስተያየት ነው። እያንዳንዱ የሃይማኖት ሰባኪ ስለራሱ ሃይማኖት ታላቅነት ብቻ ይናገራል። የሃይማኖቱንም ቅንነት ያረጋግጣል። ...በእውነቱ ከማንኛዎቹም ሃይማኖቶች ጠቃሚ የሆኑ መንፈሳዊ ፍሬዎች መኖራቸውን አልካድኩም። በአንድ ክፍል ሆኜ ሌላውን ዋጋ የለውም የምልበት መረጃ ግን ፈጣሪ ያውቃል አላገኘሁም። ... ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችን የተቀበሉ ያገሬ ልጆችን ሁሉ በአንድ አይነት የወንድምነት መልክ እያየኋቸው ለመኖር ቆረጥሁ።"* ይላል አልወለድም ስለ ሃይማኖት በሰፊው ሲያትት።

ይህን የአልወለድምን የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮች የሀገሩን ልጆች በወንድምነት የማየት እምነት የተለያዩ የሃይማኖት ዘርፎች ሰባኪያን 'የኛን ሃይማኖት ተከተል' እያሉ በ እምነት ሲፈታተኑት እጅግ ሰፊ ሀይማኖታዊ የፍልስፍና ትንታኔዎችን ሰጥቷቸዋል። የትንታኔዎቹን አረፍተ ነገራት እንኳን እናበራይ ብንል እያንዳንዳቸው አያሌ አንቀፆች ይወጧቸዋል። ለቅምሻ ያህል ግን ይኸው ይበቃል።

**ሐ. አልወለድምና ስርዐተ መንግስት**

*“… አንድ የሬቮሉሽን /አብዮት/ ድርጅት ስልጣን ሲይዝ ያለፈውን መንግስት ‘ጨቋኝ፣ የህዝብ ጠላት፣ አረመኔ!’ ማለቱ የተለመዱና የማይታለፉ ቃሎች እንደ መሆናቸው መጠን የማርሻል ጃፈርሶ የፕሮፓጋንዳ ሰዎችም ‘የኢይዝራኤሎስ ህዝብ ሆይ! በጨቋኞች፣ በቆራጭ ፈላጮችና በዘራፊዎች እጅ ተጨብጦ የነበረው መብትህ ጥቅምህና ነፃነትህ ዛሬ ተለቀቀ። ደስ ይበልህ! የድሮውን የጭቆናና ያውሬነት አገዛዝ ለመመለስ የሚሞክሩ የሀገርና የህዝብ ጠላቶችን ስታገኝ በያለህበት የሞት ቅጣት እንድትፈፅምባቸው … ያለፍርድ ሲያፈሱት የኖሩት ንፁህ ደም ሁሉ ተፋርዷቸዋል …”* ይላሉ ይለናል አልወለድም፣ ወደ ስልጣን የሚመጡ ተተካኪ መንግስታትን አጠቃላይ ባህሪ ሲገልፅ።

ከየካቲት 1966 ዓ/ም አብዮት በኂላ በጠመንጃ አፈሙዝ መንበረ ስልጣኑን የጨበጠውን የወታደራዊውን መንግስት አዋጅ ነበር የገለፀልን አልወለድም። “… የኢይዝራኤሎስ ህዝብ ሆይ!” የሚለውም “የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ…” ለሚለው ተምሳሌ ሆኖ ነው የቀረበልን።

ይህ አዋጅ ሌላም ተምሳሌነት አለው። በቅርብ ዘመኑ ታሪካችን ሁለት መንግስታት በፈረቃ ስልጣን የጨበጡት በጠመንጃ አፈሙዝ ነው። ሁለቱም “የኢይዝራኤሎስ ህዝብ ሆይ!…” ብለው በተለያዩ ዘመናት ያወጧቸው አዋጆች የቅርፅ እንጂ የይዘት ልዩነቶች የሏቸውም። በጠመንጃ አፈሙዝ ስልጣን የጨበጡትም የኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ኢሰፓ አገዛዝ እና የአቶ መለስ ዜናዊ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዞች ናቸው።

ለመሆኑ ማርሻል ጃፈርሶ ማን ነው? ብለን እንጠይቅ። እንደ ኢይዝራኤሎስ ስም ተምሳሌነት ሁሉ ማርሻል ጃፈርሶም ተምሳሌያዊ ገፀ ባህሪ ነው። የሚገርመው ማርሻል ጃፈርሶን የአንድ ስርአተ አገዛዝ ተምሳሌ ገፀ ባህሪ ብቻ ሆኖ አለማግኘታችን እንጂ! አልወለድም ስለ ማርሻል ጃፈርሶ ማንነት የሚከተለውን ያጫውተናል።

*“ማርሻል ጃፈርሶን አውቀዋለሁ። የህዝብ ጠላቶች እያለ ከሚፈጃቸው ሰዎች የተለየ ጠባይ በህይወቱ ሙሉ ታይቶበት አያውቅም። ካለፉት ዘራፊዎች አንዱ ራሱ ነበር። … እሱን ንፁህ ያደረጉት ያሰለፋቸው ወታደሮቹና በጁ ያሉት የጦር መሳሪያዎች ናቸው እንጂ በህግ ፊት ካለፉትና እሱ ከሚፈጃቸው ሰዎች ጋር አንድ ነው።”*

ቀዳማዩ ማርሻል ጃፈርሶ ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም እና ጓዶቻቸው በጠመንጃ አፈሙዝ ስልጣን ሲይዙ ከቀዳማዊ ሃይለስላሴ ጀምሮ በግፍ የፈጇቸው ባለስልጣናት ብዙዎች ናቸው።

ዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ አቶ መለስ ዜናዊና ጓዶቻቸው በተራቸው በጠመንጃ አፈሙዝ አራት ኪሎ ከገቡ በኂላ ደግሞ እንደ ቀዳማዩ ማርሻል ጃፈርሶ ማርሽ እያስደለቁና የፍየል ወጠጤ እያዘፈኑ አይሁን እንጂ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የፈጁዋቸው የቀዳማዩ ጃፈርሶ አገዛዝ ባልደረቦች ብዙዎች ናቸው።

*“ማርሻል ጃፈርሶ ስልጣን ጨብጦ ሁለት አመት እስኪሞላው ድረስ የህዝብ ድጋፍ ያለው ይመስል ነበር”* ይላል አልወለድም። ከዚህ በኂላ የማርሻሉ አገዛዝ ምን እንደሚመስል ሲገልፅልን እንዲህ ይላል።

*“የህዝቡም ጠቅላላ ኑሮ ሰላም ከማጣቱና የፍርሃት መንሰራፊያ ከመሆኑ በቀር ከድሮው በምንም አልተሻሻለ። የግል ጋዜጦች ሁሉ በወታደራዊ መንግስት ስልጣን ስር ከመዋላቸው*

*አንዳንዶችም ከመዘጋታቸው በላይ፣ ስለ ህዝቡ ኑሮ ጥቂት ማጉረምረም የሚያሳዩ የፖለቲካ ሰዎች ሁሉ እየተያዙ ያለፍርድ ይታሰሩ ጀመር። አንድ ሰው በፅሁፍም ሆነ በንግግር፣ ወታደራዊውን መንግስት ከማመስገንና የድሮዎቹን መሪዎችና ሀብታሞች ከመንቀፍ ያለፈ ሀሳብ የመግለፅ መብት አጣ። …ማንም ሰው ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ የመቃወሚያ ቀርቶ የአቤቱታ ድምፅ እንዲያሰማ የማይፈቀድለት ሆነ"*

እግዚኦ! በአንተ መጀን አቤ! አዎ እውነት ተናግረኻል! አዎ! እውነት ፅፈሃል!! አዎ፣ ይህ በቀዳማዩ ማርሻል ጃፈርሶ ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ዘመነ አገዛዝ የታየ ሀቅ ነበር። አዎ! ይህ በዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ አቶ መለስ ዜናዊ ዘመነ አገዛዝ እየታየ ያለ ሀቅ ነው!!

ስለ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርና ስለ አምባገነናዊ አገዛዝ ሰፊ ማብራሪያ ከሰጠው አልወለድም ውስጥ የሚከተለውን አስደናቂ አገላለፅ እናገኛለን።

*"የኛዎቹ አዲስ መንግስት መስራቾች በሃይል ጭጭ አድርገው እየገዙን እያየን፣ ሀገራችንን ከጭቆና አገዛዝ ወደ ነፃነት መራናት እያሉ ይፎክሩብናል።"*

ቀዳማዩ ማርሻል ጃፈርሶ መንግስቱ ሃይለማርያምና ጓዶቻቸው ለአስራሰባት አመት በዚህ መዝሙራቸው አደንቁረውን ነበር። የዜማው ቅርፅና ይዘት ሳይቀየር ዘማሪዎቹ ብቻ ቦታ ተለዋውጠው እነሆ ዳግማዊው ማርሻል ጀፈረሶ አቶ መለስ ዜናዊና ጓዶቻቸው ደግሞ በተራቸው ካለፉት ሃያ አመታት ጀምሮ እያላዘኑብን ይገኛሉ። ይህ እስከመቼ ይቀጥል ይሆን? ከዚህ የሚታደጉንስ ሳልሳዊው ምኒልክ ወይም ዳግማይት ጣይቱ የት ይሆን ያሉት?!

**መ. አልወለድምና የጦር ሃይሉ**

አልወለድም በማርሻል ጃፈርሶ አገዛዝ ላይ አምፆ ሲነሳ በማርሻሉ እዝ ስር ለሚገኘው ሰራዊት የሚከተለውን መልእክት አስተላልፎ ነበር።

*"…ለግል ስልጣኑና ጥቅሙ ለሚታገል አንድ ማርሻል ክብር ብላችሁ የወገናችሁንና የራሳችሁን ደም በከንቱ ብታፈሱ የምታገኙት ክብርና ጥቅም የለም። እኛ አሁን የምንጠይቀው የገበሬውንም፣ የነጋዴውንም፣ የፀሀፊውንም፣ የወታደሩንም፣ የባለ ኢንዱስትሪውንም፣ የጥበበኛውንም መብት በትክክል ለመጠበቅ የሚችል ሰላማዊ መንግስት እንዲቋቋም … እንጂ ማንኛውንም ክፍል የሚጎዳ አጥቂ ስራ ለመስራት አይደለም። ስለባልቴቶችና ሽማግሌዎች፣ ስለ ህፃናትና እህቶች ብላችሁ ተለመኑን። አደገኛ የሆነውና ለውድቀቱ ቀላል መድሃኒት የማይገኝለት የርስ በርስ ጦርነት በሀገራችን ላይ እንዳይደርስ ተጠንቀቁ።*

*"… ወንድሞቻችን ሆይ! እኛ የምንጠይቀው ሁላችንም በየቦታችን ተግባራችንን እየፈፀምን፣ አንዳችን ላንዳችን ተቃዋሚ ሳንሆን ለመኖር እንጂ አንዱን ክፍል ጥለን ሌላው እንዲፈነጭበት አይደለም።*

*"… ወታደራዊ ግዳጅ አገርን ከወራሪ ጠላት መጠበቅ እንጂ የገዛ ወገንን ለአንድ ማርሻል ለማስገዛት ከወገን ጋር መዋጋት አይደለም። ልብ ብላችሁ አስታውሱ! እነዚህ የግል ጥቅምና የስልጣን ፍላጎት ያወራቸው አለቆቻችሁ ለግል ፍላጎታቸው ሲሉ… ሀገራችሁንና ፀጥታችሁን እስከመጨረሻው እንዳያበላሹ ንቁባቸው።"*

በዳግማዊው ማርሻል ጃፈርሶ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ እዝ ስር የምትገኘው ሰራዊት ሆይ!

በመካከለኛው ምስራቅ የነደደው የህዝብ አመፅ ሰደድ እሳት ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ ኢትዮጵያ መድረሱ አይቀሬ ነው። ያኔም ውስጥ ለውስጥ ተዳፍኖ የቆየው ቋያ ቢንተገተግና የጦቢያ ልጅ ሁሉ የግፍና የዘረኝነት አገዛዝ በቃኝ ብሎ እንደ ንብ በተምና ቢነሳ አፈሙዝህን ከቶም በወገንህ ላይ አትደግን!! ይህንን ታላቅ የአልወለድምን ከመቃብር ጥሪ አስታውስ!! ከግበፃዊያን የሙያ ባልደረቦችህም ተማር!!

__*መሸበቢያ*__

አልወለድም ባህር ነው። በዚህ ባህር ውስጥ ህይወት አለ። በዚህ ባህር ውስጥ ምስጢራት ይገኛሉ። የምስጢራቱን ቁልፍ ለማግኘት ከባህሩ መጥለቅ ግድ ይላል። ምስጢራቱ ለወጣቱ ትውልድ ሲገለጡም በጦቢያ ሰማይ ፀሀይ ትወጣለች።

አልወለድም በዚህ ዘመንና በዚህ የታሪክ ፈተና ወቅት ትንታግ ከሆነው የኢትዮጵያ ወጣት እጅ በሰፊው መግባት ይኖርበታል። መፅሀፉን የማባዛትና የማሰራጨት መብት የማን እንደሆነ አላውቅም። ግን መሰራጨቱ አጣዳፊና ወቅታዊ ሆኖ ይታየኛል። አልወለድም በወጣቱ ትውልድ ውስጥ ብዙ ጉድ የመውለድ ሃይል አለውና!

ቅኝቱን የማበቃው በሚከተለው የአቤ ጎበኛ ታላቅና ዘለዓለማዊ ዕውነት አባባል ይሆናል።

*"... በእውነት ነፃ ለመውጣት እድል እንዳለን ተስፋ አደርጋለሁ። ከእንግዲህ ወደ ነበርንበት ባርነት የምንመለስ ከሆነ ግን አሁንም ባልወለድ፣ ሌላው ኢትዮጵያዊም ባይወለድ በተሻለ ነበር።*

**"ግን ተስፋ አንቁረጥ። አንድ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ሆነን ተፈጥረናልና!"**

በያለንበት ቸር ይግጠመን!

*መስፍን ማሞ ተሰማ*
*ሚያዚያ* 2003 *ዓ/ም*
(ኤፕሪል 2011)

ሲድኒ
አውስትራሊያ

__*ማስታወሻ*__

*የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የጆርጅ ኦርዌልን 'አኒማል ፋርም' መፅሀፍ 'የእንስሳት አብዮት' በሚል ወደ አማርኛ የመለሰው ሲሆን መፅሀፉ ከኤፕሪል 17/2011 ጀምሮ ለህዝብ ይቀርባል። የእንስሳት አብዮትን መፅሀፍ ለማግኘትም ሆነ ወይም በዚህ ፅሁፍ ላይ ለሚኖርዎት ግላዊ አስተያየት እነሆ የኢሜል አድራሻ፣* msfntessema@yahoo.com.au